# በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ

**ዮሐ.4:5 ስለዚህ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው ስፍራ አጠገብ ወደምትሆን ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ፤**
**6 በዚያም የያዕቆብ ጕድጓድ ነበረ። ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ።**
**7 ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም። ውኃ አጠጪኝ አላት፤**

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ለዚህች ሴት ስለዘላለማዊ ውኃ (ስለመንፈስ ቅዱስ) እና ሌሎች እያስተማራትና ህይወቷን እየነገራት ከዚህች ሴት ጋር ንግግሩን ቀጠለ። እዚህ ጋር አንድ ነገር አስተዋልሁ፤ ኢየሱስ ስለራሷ ከነገራት በኋላ ይህች ሴት የምትለውን አዳምጡ፤

**ዮሐ.4:20 አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም። ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው።**

አሁን እዚህ ጋር ተመልከቱ፥ ይህች ሳምራዊት ሴት ለኢየሱስ፡ “*አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፥ እናንተም (ኢየሱስ ከአይሁድ ወገን ነበረና አይሁድን ማለቷ ነው) ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው።*” እዚህ ጋር በዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች በረከትንና ጽድቅን ፍለጋ፥ እንዲሁም ለስግደትና ለጸሎት ወደ ተለያዩ ስፍራዎች (እንዲሁም ተራራዎች) ሲሄዱ ያለውን ተመለከታችሁ። ሰዎች እስካሁኑ ዘመን ድረስ ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት የተናገራትን ነገር አላስተዋሉም።

ሙስሊሞች በየአመቱ ከተለያየ የዓለም ክፍል ወደ መካ ይፈልሳሉ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማኞች ወደ ተለያዩ ስፍራዎች አመታትንና ወራትን እየቆጠሩ ይሄዳሉ።

*ነገር ግን ኢየሱስ ምን እያለ ነው ያለው?*

**21 ኢየሱስም እንዲህ አላት። አንቺ ሴት፥ እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል።**

*ጊዜ ይመጣል እያላት ነው፥ ማንም በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም የማይሰግድበት ጊዜ፥ ወይም ማንኛውም ሰዎች አመታትና ወራትን ጠብቀው ለመስገድ የሚሄዱባቸውን ማንኛውም ቦታ ማለቱ ነው። ቀጠለና እንዲህ አላት፡*

**22 እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።**

አሁንም ብዙዎች ተአምራትን ስላዩ ብቻ አልያም ሀይማኖታዊ ግዴታዎችን ወይም ልማዶችን ለመፈጸም ብቻ ወደ እነዚህ ስፍራዎች እየሄዱ የሚያደርጓቸውን ነገሮች አሰባችሁ። ኢየሱስም “*እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን*” አላት። እርሱ ከአይሁድ ወገን እንደሆነና ዓለምን ለማዳን እንደመጣ መዳንም በእርሱ ውጪ በማንም እንደሌለ (ሐዋ. 4፡12) እያሳሰባት ነበር።

*ቀጥሎም ኢየሱስ ይህም የሚሆነው እንዴት እንደሆነ ሲነግራት፡*

**23 ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤**

**24 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።**

ትክክለኛውን የአዲስ ኪዳን መንገድ ነገራት፡ “*ለአብ መስገድ ከፈለግሽ ትክክለኛው መንገድ በእውነትና በመንፈስ መስገድ ነው አላት። ይህም ዘመን ይመጣል እንደዚህም የሚያደርጉት እነርሱ እውነተኞች ናቸው*” እያላት ነው። በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 14 ከቁጥር 6 ላይ ኢየሱስ “እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፥በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፤” ብሎ እንደተናገረው እንዲሁ ለዚህችም ሳምራዊት ሴት እንዲሁም ለሁላችን፥ “እውነት በሆንኩት በእኔ፥በአባቴም መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ለአብ ልትሰግዱለት አብ እንዲህ ያሉትን እውነተኞች ይፈልጋል” እያለን ነው።

ኢየሱስ “*ጊዜ ይመጣል*” አለ ይህም ጊዜ አሁን ነው። እግዚአብሔር አብ ስለዓለሙ ሁሉ መድኀኒት ሊሆን ልጁን ኢየሱስን ልኮ ቤዛ አድርጓል፤ *መጋረጃውም ተቀድዷል*፥በኢየሱስም ደም በኩል ወደ አብ መግባት ሆኖልናል። በተጨማሪም በነብዩ በኢዩኤል “*መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ*” ተብሎ የተጻፈው ቃል ከጌታ ሞትና ትንሣኤ እንዲሁም እርገት በኋላ ተፈጽሟል። ስለዚህም “*ይመጣል*” አላት። ጳውሎስም እንደመጣና እኛም እየኖርንበት እንደሆነና የማይኖሩበትም ሊኖሩበት እንዲገባ ሲያስረዳ “*እኛ በመንፈስና በእውነት የምንመላለሰ*” አለ።

ለዚህም ነው ሴቲቱ መሲሑ እንደሚመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ያስተምረናል ያለችው።

**25 ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።**

እንግዲህ መሲሑ መጥቷል፤ ሁሉን አስተምሮናል፤ ሌላውንም መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ሁሉን ያስተምራችኋል አለ፤ መንፈስ ቅዱስም መጥቷል ሁሉንም እያስተማረንም ነው። አሁንም የሚናገረን እርሱ ነው።

**26 ኢየሱስ። የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።**

የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ሻሎም።

ኢዩ.2:28፤ ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ጕበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ :29፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፤ 30፤ በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ፥ በታች በምድርም ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ። 31፤ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ፥ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣል። 32፤ እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥የምስራች የሚሰበከላቸው ይገኛሉ።

ሐዋ.2:1 በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ 2 ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።:3 እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። 4 በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። 5 ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤

ማቴ. 27:51 እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤

2ቆሮ.3:13 የዚያንም ይሻር የነበረውን መጨረሻ ትኵር ብለው የእስራኤል ልጆች እንዳይመለከቱ፥ በፊቱ መጋረጃ እንዳደረገ እንደ ሙሴ አይደለንም።

2ቆሮ.3:16 ወደ ጌታ ግን ዘወር ባለ ጊዜ ሁሉ መጋረጃው ይወሰዳል።

2ቆሮ.3:18 እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።

ዕብ.10:19-20 እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፥

ፊል3:3 እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።

2ቆሮ.5:2 በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥

1ጢሞ.2:7 እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና በእውነትም የአሕዛብ አስተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤ እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም።

ኤፌ5:9-10 የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤

በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነ ሙሉነህ አዲሱ

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።

by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com